ቁጥር. OFAG.F.05.1/66
ቀን. 07/8/2012

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA OFFICE OF THE FEDERAL AUDITOR GENERAL

ለ ክቡር አቶ ላቀ አያሌው

የገቢዎች ሚኒስትር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- <u>የሚኒስቴር መ/ቤቱን የ 2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲትን ይመለከታል፡፡</u>

በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 15 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 16 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ

የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር

የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ
ኦዲተር ሪፖርት

ሚያዝያ/2012

አዲስ አበባ

የገቢዎች ሚኒስቴር
የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲተር ሪፖርት

የገቢዎች ሚኒስቴር የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ ሊሰበሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሠረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 (እንደተሸሻለው 1146/2011) ለመቤታችን በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት እንዲደረግለት በደ.ቁ2.4/616/12 የካቲት 27 ቀን 2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለመ/ቤታችን ያቀረበውን የሂሳብ መግለጫ የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን እና የዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ስልት በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሣብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት የሚኒስቴሩ የተጠቃለለ ሂሳብና 11 ቅ/ጽ/ቤቶቹ ያቀረቧቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣
- የገቢ ሂሳብ መግለጫ፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ መግለጫ፣
- የተከፋይ ሂሳብ መግለጫ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ተከናውኖ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1. ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2010 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ/ ከ2010 በጀት ዓመት የ 12 ወራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው ጠቅላላ ሽያጭ/ገቢ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት በመኖሩ እና ለልዩነቱም አሳማኝ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምክንያት ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ *በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 119,466,035.00 መገኘቱ፣
2. አጠቃላይ ተቀባይነት ባገኘው የሂሳብ አያያዝ ስልት (GAAP) መሰረት ያለፈው ዓመት በመጋዘን የቀረ የሚሸጥ ዕቃ (ending inventory) ሚዛን ለቀጣይ ዓመት የመነሻ ሚዛን ሆኖ በዘመኑ ግዢ ላይ በመደመር በዘመኑ ለሽያጭ የሚቀርብ እቃ(goods available for sale) ሆኖ መያዝ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ

በ2009 የግብር ዘመን የሂሳብ መግለጫ ላይ በአመቱ መጨረሻ ሳይሸጥ የቀረ *ዕቃ*(ending inventory) በ2010 የግብር ዘመን ላይ እንደ መነሻ ሚዛን(beginning inventory) አድርጎ በተመሳሳይ መጠን ማዞር ሲገባው ከፍ እንዲል በመደረጉና ለልዩነቱም በቂ ማረጋገጫ ባለመቅረቡ ሳይሰበሰብ የቀረ ንግድ ትርፍ ግብር ***በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በድምሩ ብር 3,959,250.66 መገኘቱ፣

3. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 27 ንኡስ አንቀጽ (1) ሀ-ነ በተገለጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች የተዘረዘሩ ቢሆንም ከገቢ ላይ መቀናነስ የሌለባቸው ወጪዎች እንዲቀነሱ የተደረገ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ***በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በድምሩ ብር 41,419,832.42 መገኘቱ፣
4. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 61 በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 10 በመቶ ግብር እንደሚከፈልበት እንዲሁም ሐምሌ 30/2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር መመሪያ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 መሰረት ከ2006 በጀት ጀምሮ ኩባንያዎች ያገኙትን ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት እና ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርቡ በሚያዘው መሰረት ማስረጃውን ማቅረብ እንዳለባቸውና ማስረጃውን ያላቀረቡ ኩባንያዎች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖች እንዳከፋፈሉ ተቆጥሮ ግብሩን መክፈል እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዮች ያገኙትን ትርፍ የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ያሳደጉ ስለመሆኑ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ በኦዲት ወቅትም ማስረጃው ተጠይቆ ሊቀርብልን ባለመቻሉ ***በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች*** በድምሩ ብር 2,420,512.74 ያልተሰበሰበ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር መኖሩ፣
5. በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 4010/2009 አንቀጽ 41 ቁጥር 3 መሰረት በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው ለሚቀንስ ሀብት የተደረገ የጥገና ወይም የማሻሻያ ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ከ20 በመቶ የሚበልጥ ከሆነ የጥገናው ወይም

የማሻሻያው ሙሉ ወጪ በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ እንደሚካተትና የእርጅና ቅናሽ ስሌት መሰረት ወጪ እንደሚያዝለት ይገልፃል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶች ግብር የሚከፍሉ ድርጅቶች ለጥገናና ማሻሻያ ብለው ከገቢ ላይ የቀነሱት ወጪ፤ ለእርጅና ቅናሽ መሰረት ከሆነው የዕቃ ዋጋ ሃያ ከመቶ በላይ መሆኑ እያታወቀ ወጪው በእርጅና ቅናሽ ደንብ መሰረት ካፒታላይዝ በማደረግ የእርጅና ቅናሹ እንደ ወጪ መያዝ ሲገበው ወጪውን ሙሉ በሙሉ እንዲያዝ በመደረጉ ምክንያት ያልተሰበሰበ ፍሬ ግብር *በ 4 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 858,198.13 መገኘቱ፣

6. በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 22/ሐ/ እና አንቀጽ 25/1/ በግብር ዓመቱ የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማስገኘት በግብር ዓመቱ ጥቅም ላይ ላዋላቸው እና ዋጋቸው ለሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የንግድ ስራ ሀብቶች ዋጋቸው በቀነሰው የገንዘብ መጠን ልክ የእርጅና ቅናሽ ማድረግ እንደሚቻል በተገለጸው መሰረትና እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 39 ላይ ዋጋቸው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው በሰንጠረዥ በተጠቀሰው የእርጅና ቅናሽ ምጣኔ መሰረት መሆን እንዳለበት ቢገለጽም *በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች* የእርጅና ቅናሽ ስሌቱ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት የተሰላ ባለመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ፍሬ ግብር በድምሩ ብር 23,315,522.67 መገኘቱ፣

7. በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ክፍል አስር አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 በተገለጸው መሰረት እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀን 06/ህዳር/2007 በቁጥር 6.0/18/07 ባስተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩንና ንግድ ፈቃዱን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በህግ ግብርን ቀንሶ የማስቀረት ስልጣን የተሰጣቸው ድርጅቶች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና ንግድ ፈቃድ ካላቀረቡ ድርጅቶች ግዢ ሲፈጽሙ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30 በመቶ መቀነስ ሲገባቸው 2 በመቶ ብቻ ተቀናሽ ያደረጉ በመሆኑ በወቅቱ ያልተሰበሰበ ቅድመ ግብር *ከ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 27,055,379.69 መኖሩ፣

8. ግብር ከፋይ ድርጅቶች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስባቸው ቅድመ ግብር የሸያጫቸውን 2% መሆኑ ወይም ይህም ማለት በሌላ አገላለጽ ሽያጩ = (ቅድመ

ግብር X 50) መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ግብር ከፋዮቹ ያሳወቁት የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ ከዚህ በታች በመሆኑና ለልዩነቱም በቂ ምክንያት ባለመቅረቡ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር *በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 1,280,583.94 መኖሩ፣

9. በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 96 መሰረት ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር ተቀንሶ በሚያዝበት ጊዜ ግብሩን ቀንሶ የሚይዘው ሰው ክፍያውን ለሚቀበለው ሰው ግብር ተቀንሶ መያዙን የሚረጋግጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ *በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች* የተመዘገቡ ግብር ከፋዮች የቅድመ ግብር ዝርዝር ማስረጃ/ደረሰኝ ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ሳያቀርቡ ከዓመታዊ ግብራቸው ላይ በድምሩ ብር 1,661,567.54 ቅድመ ግብር እንዲቀነስ በመደረጉ ያልተሰበሰበ ትርፍ ግብር መገኘቱ፣
10. የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 21 እና 26 ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው በደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት በአግባቡ ባለመሰላቱ እና ታክስ ከፋዮቹ ባቀረቡት ማስረጃ መሰረት እንዲሰበሰብ ባለመደረጉ በ5 ቅ/ጽ/ቤቶቹ መሰብሰብ የነበረበት የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ ብር 12,890,784.95 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
11. ግብር ከፋይ ድርጅቶች ባቀረቡት የ2010 በጀት ዓመት የንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የተገለጸው የዓመቱ ጠቅላላ የግብዓት ግዥና የደመወዝ ወጪ ካቀረቡት የ12 ወራት የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ጋር ሲነፃፀር በትርፍና ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው የዓመቱ ጠቅላላ የግብዓት ግዢና ደመወዝ ወጪ የበለጠ በመሆኑ ምክንያት *በ3 ቅ/ጽ/ቤት* ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 25,551,460.91 ያለ መሆኑ፣
12. ግብር ከፋዮች ባቀረቡት በንግድ ሥራ ግብር ማሳወቂያና በተጨማሪ እሴት ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው የዓመቱ ጠቅላላ ሽያጭ እና በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የቀረበው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማጠቃለያ ሪፖርት (Z-Report) ሽያጭ ጋር ሲነፃፀር በማስታወቂያዎቹ የተመለከተው ያነሰ በመሆኑና ለልዩነቱም አሳማኝ ምክንያት ባለመቅረቡ *በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች* በልዩነቱ ያልተሰበሰበ ንግድ ሥራ ገቢ ግብርና ተዕታ ብር 1,208,331.45 መኖሩ፣
13. በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 23 1 እና 2 ላይ በተቀመጠው መሰረት ግብር ከፋዩ የወሰደው ብድር ወይም ሌላ ዕዳ የንግድ ስራ ገቢውን ለማግኘት ተግባር እስካዋለው ድረስ እንዲሁም የወለዱ መጠን በብሄራዊ ባንክ እና በንግድ ባንኮች መካከል ከሚታሰብ የወለድ ምጣኔ ከ 2 ፐርሰንት ያልበለጠ ከሆነ የወለድ ወጪ እንደ ወጪ እንደሚያዝለት ይደነግጋል፡፡ *በጅማ ቅ/ጽ/ቤት* ግን 2 ግብር

ከፋች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫ ላይ ከአበዳሪ ተቋማት የተበደሩት ብደር ስለመኖሩ በሀብትና ዕዳ(balance sheet) ላይ የብድሩ መጠን ሳይገልጹ ወይም ሳያሳውቁ እንዲሁም ለንግድ ስራቸው የሚሆን ብድር ከአበዳሪ ድርጅቶች ስለመውሰዳቸው የሚያረጋግጥ የብድር ውል ስምምነት ሳይኖር ድርጅቶቹ የወለድ ወጪ ብር 494,712.03 ከገቢ ላይ ያቀናነሱ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር ብር 148,413.61 መኖሩ፣

14. በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 ክፍል አስር አንቀጽ 88/1/ ማንኛውም ቀጣሪ ከመቀጠር የሚገኝ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለተቀጣሪው በሚከፈልበት ጊዜ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 11 በተደነገገው መሰረት ተፈጻሚ የሚሆነውን የግብር ምጣኔ መሰረት በእያንዳንዱ ክፍያ ጊዜ መከፈል የሚኖርበትን የገቢ ግብር ከጠቅላላው ክፍያ ላይ ቀንሶ ማስቀረት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ *በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት* ግን 2 ድርጅቶች ከሰራተኞች ላይ ተቀናሽ ካደረጉት የሥራ ግብር ላይ በድምሩ ብር 90,810.58 ገቢ ያላደረጉ መሆኑን፣
15. ከ2009 የግብር ዘመን ወደ 2010 የግብር ዘመን ቅድመ ክፍያ የዞረ እና በግብር ዘመኑ ገቢ የተቀናነሰ ቅድመ ክፍያና በ2010 በጀት ዓመቱ በቅድሚያ ክፍያ የተመዘገበው በትክክል ተሰልቶ ወደሚቀጥለው በጀት ዓመት የተላለፈው ጋር ልዩነት በመኖሩ *በምሥራ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከ/ቅ/ጽ/ቤት* በ 4 ግብር ከፋዮች ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ፍሬ ግብር ብር 1,964,646.89 እና ያልተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 24,489.36 በድምሩ ብር 1,989,136.22 መኖሩ፣
16. ግብር ከፋዮች በ 2010 የግብር ዘመን የድርጅቱ የሆነ ንብረት በብር 16,521,739.10 በሽያጭ ሲያስተላልፉ በአዋጁ አንቀጽ 7-1(ሀ) መሰረት ተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ ሲገባው *በድሬዳዋ ቅ/ጽ/በቤት* ያልተሰበሰበ ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 2,478,260.87 መኖሩ፣

በአጠቃላይ ከተ.ቁ1 እስከ 16 በተገለጹት ምክንያቶች በወጡት አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ያልተሰበሰበ ብር 265,794,081.38 መኖሩ፣

17. የትርፍ ሰዓት ክፍያና ማካካሻ አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 133/2010 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የትርፍ ሰዓት ስራ ለማሰራት የሚፈልግ የሥራ ኃላፊ የትርፍ ሰዓት መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ እንዳለበት እና በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 1-8 የትርፍ ሰዓት ስራ በዕቅድ በተያዘው ስራ ውስጥ ያልተያዘ ከሆነ በመደበኛ ስራ ውስጥ ተካቶ ሊሰራ ያልቻለበትን ምክንያት ዘርዝሮ ከጥያቄ ጋር ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለት ቅ/ጽ/ቤቶች የትርፍ ሰዓት ክፍያ መመሪያውን ተከትሎ ያልተፈጸመ በመሆኑ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በድምሩ ብር 88,663.50 መኖሩ፣

18.የመንግስት ሰራተኞች የቀን ውሎ አበል መመርያ ሰኔ/2004 ዓ.ም በወጣው በክፍል 2 አንቀፅ 5/1/ሀ-ሰ/ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ውጭ ወደ ሆነ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው የክልላዊ ከተማ፣ የዞን ከተማ፣ የወረዳ ከተማና የከተማ አስተዳደሮች እንዲከፈል የተመደበውን የውሎ አበል መጠን መከፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ *በጅማ ቅ/ጽ/ቤት* በተለያዩ ምክንያቶች በዋናው መ/ቤት እና በሌሎች ስልጠና ሰጪ አካላት በቢሾፍቱ የማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በሚዘጋጁ ስልጠናዎች ላይ እንዲሳተፉ ሰራተኞቹን የላከ ሲሆን የሰራተኞችም የምግብና የመኝታ ወጪ የሚሸፈነው ስልጠናውን ባዘጋጀው አካል መሆኑን እና ቅ/ፅ/ቤቱም ለሰልጣኞቹ ሊሸፍን የሚገባው ወጪ የትራንስፖርት ወጪ ብቻ መሆን እንዳለበት ስልጠናውን ያዘጋጀው አካል/ዋና መ/ቤቱ ያሳወቀ ሲሆን፤ ቅ/ጽ/ቤቱ ግን በድጋሚ ለሰራተኞቹ ሙሉ የውሎ አበል በድምሩ ብር 44,331.00 መክፈሉ፤

19.ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 5 አንቀጽ 24.1 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች አስቀድመው ማቀድ እስከ ተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈፀም አለባቸዉ ብሎ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚዉሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መግዛት ይቻላል ብሎ የተደነገገ ቢሆንም በአንቀጽ 24.12 መሰረት በዚህ አንቀጽ ለመጠቀም ሲባል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት አይኖርባቸውም ብሎ ይደነግጋል፡፡ *በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች* በበጀት ዓመቱ አንድ አይነት ዕቃዎች የግዥ መጠናቸው ከብር 200,000.00 በላይ መሆኑ እየታወቀ በጨረታ ላለመግዛት ሲባል ያለ በቂ ምክንያት ግዥው በተለያየ ጊዜ ተከፋፍሎ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ እንዲገዛ የተደረገ የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ በድምሩ ብር 3,832,170.10 መኖሩን፣

20.በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 56/1 መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ቢያንስ ሶስት አቅራቢዎች በውድድሩ ላይ እንዲሳተፉ መጋበዝ እና እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ታህሳስ 2008 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት ለዕቃ ግዥ ከብር 5,000.00 እስከ ብር 200,000.00 እንዲሁም ለአገልግሎት ግዥ እስከ ብር 150,000.00 የሚፈጽሙ ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ *በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች* በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ አቅራቢዎችን በማወዳደር ግዢ እንዲፈጸም መደረግ ሲገባው ያለ በቂ ምክንያት

የተፈጸመው የግዥ ወጪ ብር 459,336.17 ከአንድ አቅራቢ እንዲገዛ የተደረገ መሆኑን፣

21. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ *በ 2 ቅ/ጽ/ቤቶች* የኮንትሮባንድ መከላከል ዙሪያ ስልጠና በተሰጠበት ወቅት ለምግብ፣ ለአዳራሽ ኪራይ፣ ለመኝታ እና የሻይ ቡና አገልግሎት ለተከፈለው ክፍያ እና በተደረገው ስብሰባዎች ላይ ለተከፈለው የመስተንግዶ ክፍያ በድምሩ ብር 2,656,025.96 አስፈላጊ ማስረጃዎች ከክፍያው ትዕዛዝ ጋር አለመቅረባቸው እየታወቀ ክፍያው እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑን፣
22. በግዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ማንኛውም ወኪል በሚፈጽመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት በየወሩ ቀንሶ ያስቀረውን ታክስ በሚቀጥለው ወር ውስጥ ለታክስ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንደሚኖርበት ይገልጻል፡፡ *በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት* የተፈጸመው የመኪና ኪራይ ግዥ የተጨማሪ እሴት ታክሱን ጨምሮ ሙሉ ክፍያውን ብር 300,000.00 የከፈለው ሲሆን ነገር ግን ቅ/ጽ/ቤቱ ከተከፋይ ሂሳቡ ላይ በቅድሚያ ተቀናሽ መደረግ የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ብር 39,130.43 ክፍያ በሚፈጸምበት ጊዜ ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑን
23. በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ንዑስ አንቀፅ 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋና ደረሰኝ መሆን ሲገባው *በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት* ለተለያዩ ክፍያዎች በሚል አርዕስት የሚታይ በድምር ብር 11,629,690.79 የግብር ተመላሽ ክፍያ ሲፈፀም ተከፋዩ ገንዘቡን ስለመቀበሉ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
24. በታክስ አስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 50 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ግብር ከፋይ ታክስ ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ባሉ ሶስት አመታት ውስጥ ተመላሽ ካለው ይመለስ ዘንድ ለባለስልጣኑ ማመልከት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 28 ንኡስ አንቀጽ 2 ቁጥር 1 ላይ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ታክስ ከፋዩ የራሱ ታክስ ስሌት ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 5 ዓመት ውስጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ በማንኛውም ሁኔታ የታክስ ስሌት ማሻሻያ ሊያደርግ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ *በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት* ተመላሽ የተደረጉ ሂሳቦች የተጠቀሰውን የአዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ ለግብር ከፋዮች ግብራቸውን ከከፈሉበት ጊዜ ከሶስት እና ከአምስት አመታት በላይ ለቆየ ተመላሽ ሂሳብ ብር 596,006.52 ተመላሽ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን፣

25.በ2011 በጀት ዓመት የገቢዎች ሚኒስቴር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ተጠቃሎ መቅረብ ሲገባው ፤ የተጠቃለለው ሪፖርት

- በቅርንጫፍ መ/ቤቶች የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸው ጠቅላላ በእጅ እና በባንክ ያለ ገንዘብ ድምር ከተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ጋር ሲነጻጸር በተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸው በብር 43,036,900.70 የሚያንስ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የማጠቃለያ ሂሳብ ላይ የገቢ ሂሳብ መደብ ሪፖርት የተደረገው ገቢ በቅ/ጽ/ቤቶቹ ተዘጋጅቶ ሪፖርት ከተደረገው ጋር ሲነጻጸር በብር 204,921.18 የሚበልጥ መሆኑ፣
- በቅ/ጽ/ቤቶች ተዘጋጅቶ በተላከው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸው የተሰብሳቢ ሂሳቦች ዝርዝር ሪፖርት በሚኒስቴር መ/ቤት ከተጠቃለለው ጋር ሲነጻጸር በማጠቃለያ ሂሳብ ላይ የተገለጸው ተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩነቱ በማነስ በብር 15,561.27 እና በመብለጥ በብር 2,476.94 ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- በቅ/ጽ/ቤቶች ተዘጋጅቶ በተላከው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገለጸው የተከፋይ ሂሳቦች ዝርዝር ሪፖርት በሚኒስቴር መ/ቤት ከተጠቃለለው ጋር ሲነጻጸር በማጠቃለያ ሂሳብ ላይ የተገለጸው ልዩነቱ በማነስ በብር 269,193.19 እና በመብለጥ በብር 56,284.19 ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሰኔ 30/2010 በሂሳብ ሪፖርት ላይ የታየው በባንክ ያለ ገንዘብ ላይ ከተሰራው ማስተካካያ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 84,194,349.29 በክሬዲት በመያዙ ባንክ ያለ ገንዘብ በማነስ እንዲታይ መደረጉ፣

በገቢዎች ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት

- በግዥና ፋይናንስ አስተዳደር በቀረበ የሂሳብ መግለጫ መሰረት የባንክ ሂሳብ ዝርዝር መግለጫ (Bank Statement) ላይ በታየው የገንዘብ መጠን የባንክ ማስታረቂያ ብር 69,410,569.66 የሚታይ ሲሆን በሂሳብ ሪፖርት (Financial Report) Cash at bank Budgetary የሂሳብ ቁጥር 1000005069398 ብር

70,416,730.32 የሚታይ በመሆኑ በልዩነቱ ብር 1,006,160.66 የሂሳብ ሪፖርት በብልጫ የሚታይ መሆኑ፡-

- በገቢ ሂሳቦች አስተዳደር በቀረበ የሂሳብ መግለጫ መሰረት የባንክ ሂሳብ ዝርዝር መግለጫ (Bank Statement) ላይ በታየው የገንዘብ መጠን የባንክ ማስታረቂያ ባንክ ያለ ተቀማጭ (cash at bank deposit) ሂሳብ ቁጥር 0100191040218 ብር 7,929,528.59 የሚታይ ሲሆን በሂሳብ ሪፖርት (Financial Report) ብር 8,526,726.59 በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርት በመብለጥ ልዩነት ብር 597,198.00 የሚታይ በመሆኑ በድምር ብር 1,603,358.66 የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት በመብለጥ ማሳየቱ፣

26. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲኖረውና የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ መሰብሰብ እንዳለበት ቢገልጽም፣

- *በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች ግን ማስረጃ ሊቀርብለት ያልቻለ* ብር 27,347,821.31 የተሰብሳቢ ሂሳብ በብልጫ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
- *በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች ደግሞ* ማስረጃ የሌለው ብር 173,361,310.32 የተከፋይ ሂሳብ በብልጫ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-26 በተገለጹት ሁኔታዎች ምክንያት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የ2011 በጀት ዓመት የተጠቃለለው ሂሳብ የሂሣብ መግለጫዎች የመ/ቤቱን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት አመቱን የስራ እንቅስቃሴ በሚያሳይ ሁኔታ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንዲሁም በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት ያልተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት ትክክለኛውን ሁኔታ አያሳይም፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር

ቀን------------------------------

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

ሌሎች ጉዳዮች፣

ምንም እንኳን የኦዲት አስተያየታችንን ሊያስለውጡ ባይችሉም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና አፋጣኝ የእርምት እርምጃ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

1. የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 27 ንኡስ አንቀጽ (1)ሀ-ኘ በተገጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች ከገቢ ላይ ተቀናሽ መደረግ እንደሌለባቸው እና አንቀጽ 96 መሰረት ከአንድ ክፍያ ላይ ግብር ተቀንሶ በሚያዝበት ጊዜ ግብሩን ቀንሶ የሚይዘው ሰው ክፍያውን ለሚቀበለው ሰው ግብሩ ተቀንሶ መያዙን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀፅ 39 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ መሰረት ማንኛቸውም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ስራ ሀብት መቶ በመቶ ግዙፋዊ ህልዎት ለሌለው ሀብት የአገልግሎት ዘመን በማካፈል የሚገኘው ምጣኔ መሰረት መሰላት እንዳለበት እና አንቀጽ 41 ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ከንግድ ስራው ንብረት የተደረገ የጥገና ትክክለኛ ወጪ እንዲቀነስ እና በአንድ የግብር ዓመት ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ የተደረገ የጥገና ወይም የማሻሻያ ወጪ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ 20 በመቶ የሚበልጥ ከሆነ የጥገናው ወይም የማሻሻያው ሙሉ ወጪ በሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ ላይ እንደሚካተት እና በአንቀጽ 22 ቁጥር 1 ከሀ-ሠ የተጠቀሱ ወጪዎች ከገቢ ላይ መቀናነስ እንደሌለባቸው ይደነግጋል፡፡ *በ5 ቅ/ጽ/ቤቶች* ግን የወጪ ማስረጃና የእርጅና ቅናሽ ማስረጃ የሊዝ ዘመናና የሊዝ ዋጋ ባለመገለጹ ተቀናሽ የተደረገ ከተከፋይ ተቀናሽ ድርጅቶች ማስረጃ ሳይቀርብ ከገቢ ላይ እንዲቀናነስ ያደረጉት ወጪ በድምሩ ብር 85,069,542.00 ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 21 እና 26 ተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስከፈል በወጣው በደንብ ቁጥር 79/1995 መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ መሰረት ተመላሽ ሂሳቦች ወደሚቀጥለው ወር በትክክል ባለመተላለፋቸው በብልጫ የዞረ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ *በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች* በድምሩ ብር 3,187,874.34 መኖሩ፣

3. ሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛ በጀት ብር 1,006,134.66 ፈሰስ መደረግ የነበረበት እንዳልተደረገ እና ሂሳቡም በተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት በ5212101(ጥሬ ገንዘብ በባንክ) ላይ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ፣
4. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2011 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘው የተሰበሰበው የሀገር ውስጥ ገቢ ሂሳብ በብር 11,946,107,951.62 (11%) ያነሰ መሆኑ ፣
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2011 በጀት ዓመት የተመደበለትን የካፒታልና የመደበኛ ወጪ በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ለመደበኛ ወጪ ከተያዘው በጀት ብር 435,467,198.83(21%) ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ፣
6. የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ባለስልጣኑ ታክሱን በመክፍያ ጊዜ ላልከፈለ ታክስ ከፋይ የሚፈለግበትን ታክስ ማስጠንቀቅያ በደረሰው በ30 ቀናት ካልከፈሉ የታክስ ከፋዩ ሀብት እንዲያዝ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለታክስ ከፋዩ ሊሰጠው እንደሚችል እና በንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ያልተከፈለ ታክስ ንብረቱ ተይዞ እስከ ሚቆይበት ጊዜ የመጨረሻው ቀን ድረስ ያልከፈለ እንደሆነ ባለስልጣኑ ሀብቱን በግልጽ ጨረታ በመሸጥ ከሽያጩ የሚገኘውን ገንዘብ ላልተከፈለ የታክስ እዳን እንዲሸፍን እንደሚያደርግ ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ *በ 9 ቅ/ጽ/ቤቶች* ሳይሰበሰብ በመቆየቱ ምክንያት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደበት የግብር ዕዳ በድምሩ ብር 15,439,423,222.64 መኖሩን፣
7. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀፅ 83 ንዑስ አንቀፅ 4/ሀ መሰረት ማንኛውም የደረጃ “ሀ“ ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም የደረጃ “ለ“ ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ግብራቸውን ማሳወቅ የሚጠበቅባቸው ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን እንዲሁም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ እና በተሰጠው የመጨረሻ የታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ታክሱን መክፈል

እንዳለበት ቢደነገግም *በ 7 ቅ/ጽ/ቤቶች* የንግድ ትርፍ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እያሳወቁ ከሚከፍሉት ድርጅቶቹ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክሳቸውን ያላሳወቁ 266 ድርጅቶች መገኘታቸው፣

8. የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስተር የፌደራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም ለማሻሻል በቁጥር 2.4.6/459/08 በቀን ታህሳስ 20/2008 ባወጣው መመሪያ አንቀፅ 25 ተራ ቁጥር ሰባት ሀ ላይ እንደተገለጸው አንድ በጀት ዓመት ውስጥ ለሚካሄደው የጥቃቅን ግዥ ከብር 75,000.00 መብለጥ እንደሌለበት ቢያዝም መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ *በ ጅማ ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ* ብር 311,978.06 መኖሩ፣

9. በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 55/7 ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠርን አለመግባባት በተመለከተ በግብር ከፋዩ በኩል ለሚመጣ ቅሬታ ለማስተናገድ በአዋጁ ላይ ቅድም ተከተሎች በተቀመጡት መሰረት ከቅ/ጽ/ቤት የዕዳ ክትትል በመዝገብ ተይዘው ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተላኩ ቅሬታዎች በተደራጀ መልኩ ተመዝግበው ክትትል ተደርጎባቸው ውሳኔ የሚሰጣቸው መሆኑ፣ ውሳኔውም በአግባቡ ለቅ/ጽ/ቤት የሚተላለፍ መሆኑ እንዲሁም በቅ/ጽቶቹ የዕዳ ክትትል በመዝገብ ላይ ማስተካከያ እያደረገ ምዝገባ የሚካሄድ መሆኑን እና ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ቁጥጥር እንደሚያደርግ ሲጣራ፣

   - የ10 የግብር ዕዳ ውሳኔ በድምሩ ብር 1,190,474,878.68 በግብር ከፋዮች ቅሬታ ቀርቦበት ቅሬታው ለዋና መ/ቤት የተላከ መሆኑን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም ነገር ግን ቅሬታው ውሳኔ ተሰጥቶበት ውሳኔው ተመልሶ ለቅ/ጽ/ቤቶቹ የተላከ ቢሆንም በቅ/ጽ/ቤቶቹ የሚታወቀው ውሳኔው አሁንም በዋና መ/ቤት እንደሆነ መሆኑ፤
   - የ 20 የግብር ዕዳ ውሳኔ በድምሩ ብር 1,124,810,946.69 በግብር ከፋዮች ቅሬታ ቀርቦበት ቅሬታቸው በዋና መ/ቤት ለሚገኘው የታክስ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የተላከ መሆኑን በቅ/ጽ/ቤቶቹ ምላሽ የተሰጠ ቢሆንም የግብር ከፋዮቹ ቅሬታ በቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ተመዝግቦ የማይገኝ መሆኑን

10. በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 55/7 ከታክስ ጋር በተገናኘ የሚፈጠርን አለመግባባት በተመለከተ በግብር ከፋዩ

በኩል የሚነሳን ቅሬታ ለማስተናገድ በአዋጁ ላይ በተቀመጡት ቅድመ ተከተሎች መሰረት ከቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል ቡድን በመዝገብ ተይዘው ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተላኩ ቅሬታዎች/ይግባኞች በተደራጀ መልኩ ተመዝግበው ውሳኔ እንደሚሰጣቸው እና ውሳኔውም በአግባቡ ለቅ/ጽ/ቤቶቹ እንዲደረስ የሚደረግ መሆኑን እንዲሁም በቅ/ጽ/ቤቶቹ ዕዳ ክትትል በኩል በመዝገብ ላይ ማስተካከያ የሚደረግ መሆኑን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም ቁጥጥር ማድረጉንበሚጣራበት ወቅት፣

- 116 ቅሬታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ በዋናው መስሪያ ቤት በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የተሰጠበት ሲሆን ግብር ከፋዮቹ በውሳኔው ባለመስማማት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ክትትል ላይ እንደሆኑ በመዝገብ ተይዞ የሚገኝ ቢሆንም ነገር ግን በቅ/ጽ/ቤቶቹ የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ እና ክትትል የማይደርግበት በቅሬታ ላይ ያለ የግብር ዕዳ ውሳኔ በድምሩ ብር 1,736,893,499.86 መኖሩ፤
- 24 ግብር ከፋዮች በ 6 ቅ/ጽ/ቤቶች የዕዳ ክትትል መዝገብ ላይ በከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ላይ የሚገኙ የዕዳ ውሳኔ ተብሎ የተያዙ የግብር ከፋዮች ዝርዝር መኖራቸውን የተገለጸ ቢሆንም ነገር ግን በዋናው መስሪያ ቤት በኩል የግብር ከፋዮቹ ዝርዝርና ቅሬታ የቀረበበት የዕዳ ውሳኔ መጠን በድምሩ ብር 223,127,274.39 ተመዝግቦ የተያዘ አለመሆኑ፣

በአጠቃላይ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ የተባለ የግብር ዕዳ ውሳኔ በድምሩ ብር 1,960,020,774.25 መረጃቸው በዋና መ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች እየተናበበ የሚያዝ አለመሆኑን፣

11. በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ክፍል ዘጠኝ አንቀጽ 55/7 ታክስ ከፋዩ ቅሬታ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 180 ቀናት ውስጥ ባለስልጣኑ በቅሬታ ላይ ውሳኔ ካልሰጠ ታክስ ከፋዩ ይግባኙን 180 ቀን በተጠናቀቀ በ 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ እንደሚችል እና በአንቀጽ 56 መሰረት ይግባኝ ሊቀርበበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 83 መሰረት የይግባኝ ማስታወቂያውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱም

ሆነ ቅ/ጽ/ቤቶች ግብር ከፋዮች በዋና መ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለተወሰነባቸው የግብር ዕዳ ውሳኔ ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ያቀረቡ ግብር ከፋዮችን ዝርዝር በአግባቡ እና በተሟላ ሁኔታ መዝግቦ በመያዝ ሁኔታቸውን የሚከታተሉና በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በየቅ/ጽ/ቤቶች ለተወሰነባቸው የግብር ዕዳ ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለግብር ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ በማለት ያቀረቡ ግብር ከፋዮች መኖራቸው የተገለጸ ቢሆንም ዝርዝራቸው በዋና መ/ቤት በህግ ጉዳዮች ስር ተመዝግበው ያልተያዙ 142 ቅሬታ የቀረበበት የግብር ዕዳ ውሳኔ በድምሩ ብር 723,889,256.93 መኖሩን፣

12.በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከሀ-ሰ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳብና አንቀጽ 5 ከሀ-ሠ የተከፋይ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶ ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ መሰብሰብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ፣

- *በ 3 ቅ/ጽ/ቤቶች* በወቅቱ ያልተሰበሰበ(ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ) ከሁለቱም የስራ ዘርፎች (ከሀብት አስተዳደር እና በሀገር ውስጥ ገቢ በድምር ብር 122,064,603.64 ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣
- *በ 5 ቅ/ጽ/ቤቶች* ሰኔ 30/2011 በወቅቱ ያልተወራረደ ተከፋይ ሂሳብ በሀብት አስተዳደር የስራ ሂደትና በሀገር ውስጥ ገቢ በድምር ብር 23,818,095.57 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣